# ሁሌ በጋሪ እንሂድ?

ከአሊ አባዳማ ( የጮሬሳው )
abaydagi@yahoo.com

ልጆች ሳለን የዛሬ 40 እና 50 ዓመት በወላጅና በልጅ መካከል የነበረው ግንኙነት በዚህ ዘመን ካለው ፍፁም የተለየ ነው፡፡ በዚያ ዘመን የነበረው አመለካከት ሁሉን ነገር ቅድሚያ ለአዋቂዎችና ለእንግዶች የሚሰጥ ነበር፡፡ እኛም ተበደልን አንልም፤ ወላጅም የበደለ አይመስለውም ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ጥሩ ነገር አገኘን ከተባለም ከአዋቂዎቹና ከእንግዶቹ እንደ እድል ከተረፈ ብቻ ነው፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ ‹‹ ምርጥ ምርጡን ለህፃናት ›› የተባለ አዲስ ባህል ፋሽን ሆኗል፡፡ በመሆኑም የአባቶቼን ባህል መድገም የማልችልበት ጊዜ ላይ መሆኔን ስላወቅሁ እንደአባት ሁሉን ነገር ቅድሚያ ለልጆቼ ከመስጠት ውጭ አማራጭ የለኝም፡፡ በቀድሞው ባህል ስሌት ቢሆን እኔ እንክብካቤ የማገኝበት እድሜ አሁን በአባትነት ዘመኔ ነበር፡፡ እውነታው ግን ያኔ ልጅ ሆኜ ያጣሁትን ቅድሚያ እንክብካቤ ዛሬ ላይ ሆኜ በዚያ ዘመን የነበረው ወላጅ ያገኘው የነበረውን እንክብካቤ አጥቻለሁ፡፡ በመሆኑም በሁለቱም ዘመን ምቾችን የተነፈገ የመጀመሪያው ትውልድ ሳልሆን እንዳልቀረሁ ይሰማኛል፡፡ ይሁን እንጂ ከአጠቃላዩ የባህል ለውጥ አስተሳሰብ ውጪ ልሆን እንደማልችል ቁርጤን አውቄ በአዲሱ የለውጥ ማዕበል ውስጥ እየዋኘሁና በአዲሱ አስተሳሰብ እየቀዘፍኩ የተረጋጋ ሕይወት በመምራት ላይ እገኛለሁ፡፡

ዘመኑ የለውጥ ነው፡፡ ሁሉ ነገር በከፍተኛ ፍጥነት እየተራመደ ነው፡፡ ቁሣዊውም ይሁን መንፈሳዊው ነገር ሁሉ በከፍተኛ የለውጥ ማእበል ውስጥ እያለፈ ይገኛል፡፡ የሰው ልጅ አስተሳሰቡና ግንኙነቱ ሳይቀር ቀደም ባለው ትውልድ ከነበረው በእጅጉ ተለውጧል፡፡ ቴክኖሎጂው በከፍተኛ ፍጥነት

እየተመነጠቀ ነው፡፡ በተለይም በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ የታየው ከፍተኛ እመርታ በብዙ የህይወት እንቅስቃሴዎቻችን ላይ ካሳደረው ተጽእኖ ባሻገር የሕዝቦችን ግንኙነትና ትስስር በማጠናከሩ አለም እንደ አንድ መንደር የተቀራረበችበት ጊዜ ላይ አድርሶናል፡፡ ድሮ የሠይጣን ሥራ ተብሎ ቤተመንግሥት እንዳይገባ ውዝግብ አስነስቶ የነበረው ስልክ ዛሬ በእያንዳንዳችን ኪስ ገብቷል፡፡ ከሃያና ሠላሳ አመት በፊት ጋሪ በኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ይኖር ለነበረው ሕዝብ ያደረገውን ውለታ ባንዘነጋውም ዛሬ የትራንስፖርት ዘርፉ በከፍተኛ ሁኔታ በተለወጠበት በዚህ ዘመን መሃል አዲስ አበባ ተቀምጦ በጋሪ ካልሄድኩ ሞቼ እገኛለሁ ቢባል አያስኬድም፡፡ ጋሪው አይገኝም ማለት ብቻ ሳይሆን ሕጉም ተቀይሯልና በዋና ከተማዋ መሃል ጋሪ ማሽከርከር አይፈቀድም፡፡ በዚያ ላይ ራሱ ሕዝቡ አይፈልገውም፡፡ መንገዱ በቀርፋፋ ተሽከርካሪ እንዲዘጋጋ፣ ከተማው እንዲቆሽሽ አይፈቅድም፡፡ ስለዚህ ዘመኑ ባቀረበልን ትራንስፖርት ከመጠቀም ውጪ ሌላ አማራጭ አይኖረምን፡፡

የለውጡን ሂደት ከፖለቲካ አንፃርም ለመመልከት ብንሞክር ተመሳሳይ ነው፡፡ በአንድ በኩል ከዛሬ 20 እና 30 ዓመት በፊት የነበረውን ዓይነት ንጉሳዊ፣ ወታደራዊ ወይም አምባገነናዊ አቋም ይዞ በስልጣን መቆየት የማይቻልበት ጊዜ ነው፡፡ ዘመኑ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የበላይነት እየያዘ የመጣበት በመሆኑ በመላው ዓለም የዴሞክራሲ ሥርአት ተከታይ አገሮች ቁጥር እየተበራከተ መጥቷል፡፡ አምባገነን የሚባሉ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት አገራት መኖራቸው ባይቀርም የጊዜ ጉዳይ ሆኖባቸው ለውጡን ለመቀላቀል አፋፍ ላይ ቆመው ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የትግል ስልቱ የዚያኑ ያህል ተቀይሯል፡፡ ከሃያና ሰላሣ አመታት በፊት ሕዝቦች ጭቆናን ለመጣል ሲነሱ በጊዜው ያዋጣቸው የነበረው የትግል ስልት የትጥቅ ትግል ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ይህ ስልት ትክክለኛና ተገቢ ነበር፡፡ በነፃነት የመደራጀትና ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት ባልተከበረበት በዚያ ዘመን ያዋጣ የነበረው ይህ የትግል ስልት ግን ዛሬ በዚህ ዘመን ጊዜ አልፎበት ከመድኃኒትነቱ ይልቅ መርዝነቱ አይሏል፡፡ ሃሳብን በግልም ይሁን በቡድን በነፃ መግለጽ ፣በየትኛውም ፓርቲ

መደራጀት፣ ያለፍርሃት መሰብሰብና ተቃውሞን በሰላማዊ መንገድ መግለጽ፣ የሚያምንበትን መሪ መምረጥና መመረጥ በሚቻልበት በዚህ ዘመን ላይ ቆሞ ውጅግራና ወጨፎ መወልወል፣ መፎከርና ማቅራራት ምንይሉት ጅል ሃሳብ ሆኗል፡፡ የዘመኑ የትግል ስልት ፖለቲካ ነው፡፡ የውጊያ መሣሪያው ሃሳብ ነው፡፡ የፍልሚያ መድረኩ ጫካና ተራራ ሳይሆን የስብሰባ አዳራሽና ጠረጴዛ ሆኗል፡፡ የውጊያ ስልቱ የሃሳብ ፍልሚ፣ ድርድር ነው፡፡

እናም የትግል ስልቱ ፣ የፍልሚያ ቦታው፣ የውጊያ መሣሪያው ሁሉ ተለውጦ ባለበት በአሁኑ ወቅት በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች አዲሱን አስተሳሰብ አንግበው የፖለቲካ ትግሉን ሲቀላቀሉ አሁንም በጋሪ ካልሄድኩ ሞቼ እገኛለሁ የሚል የፖለቲካ ድርጅት መኖሩንም እየታዘብን ነው፡፡

ሰሞኑን በምርጫ ስነ - ምግባር ደንብ ዙሪያ እየተካሄደ ያለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርድር ከአገራችን የፖለቲካ ሂደት አኳያ ታላቅ ትርጉም የሚሰጠው ሲሆን ድርድሩ አንድ እውነት ፈጦ እንዲወጣ አስችሏል፡፡ ይኸውም የዚህቺን አገር ፖለቲካዊ ችግሮች በድርድር መፍታት እንደሚቻል ብቻ ሳይሆን እንደሚገባም እምነቱ ያደረገ የፖለቲካ አስተሳሰብ የበላይነትን እየያዘ መምጣቱን አመላካች ሆኗል፡፡ ለዚህ በአንድ በኩል ማስረጃ የሚሆነን ገዢው ፓርቲ ይህን አስተሳሰብ ገና ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ አንስቶ ሲያራምደው የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እየተከተለ ያለው አቅጣጫ የፓርቲውን የበሰለ አስተሳሰብ ደረጃ የሚያንፀባርቅና የሚያስመሠግነው ሆኗል፡፡ በተለይም የፓርላማ ስነ- ስርአት ሕግን፣ የፓርቲዎች ምዝገባ ሕግንና የስነ - ምግባር ደምቡን በማዘጋጀት ረገድ ያሳየው ሆደ-ሰፊነት ሊደነቅ የሚገባው ነው፡፡

በሠላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ የቆረጡ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችም ከኢህአዴግ ጋር በአንድ ክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበው የዚህችን አገር የፖለቲካ መፃኢ - እድል በመወሠን ረገድ ጉልህ ፋይዳ ያላቸውን

ሕጐችና ደንቦች ለማውጣት እየተደረገ ባለው ጥረት እየተጫወቱት ያለው ጉልህ ሚና የወደፊቱን የፖለቲካ ህይወታችንን ብሩህ የሚያደርገው በመሆኑ የላቀ ምሥጋና ሊቸራቸው ይገባል፡፡ በተለይም መኢአድ የተባለው ፓርቲ ከአሁን በፊት ይታይበት የነበረውን ግትር አቋም ወደጐን በመተው እየተካሄደ ባለው ድርድር ላይ መካፈሉ ፓርቲው ወደ ላቀ የፖለቲካ አስተሳሰብ መሸጋገሩን ጠቋሚ በመሆኑ ልዩ አድናቆትና ምሥጋና እንዲቸረው የሚያደርግ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር ጠቧል፣ ሠፍቷል በሚል ንትርክ ተጠምደው የከረሙት ፓርቲዎች በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተኰልኩለው በጋራና በአገራዊ ጉዳዮች ላይ መነጋገር መቻላቸው በእኛ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡ በተለይም የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል፣ በአገሪቱ ለፖለቲካ ትግል አመቺ ሁኔታ የለም በማለት በግንባር ቀደምትነት ሲከራከሩ የቆዩት ተቃዋሚ ፓርቲዎች መድረኩ ጠቧል፣ ሰፍቷል ማለቱን ለጊዜው ትተው በተፈጠረው መድረክ ሁሉ ተጠቅመው የበኩላቸውን አገራዊ ድርሻ ለመወጣት የወሰዱት እርምጃና እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴ በአገራችን ለተጀመረው የዴሞክራሲ ሥርዓት ማበብና መጠናከር እንደአንድ ትልቅ እርምጃ ሊታይ ይገባዋል፡፡

በአንፃሩ ‹‹ መድረክ ›› በሚል መጠሪያ የሚታወቀው ፓርቲ አሁንም መለወጥ አቅቶት ከዳር ቆሞ መንገታገቱ አሳዛኝ ነው፡፡ ፓርቲዎችንና ግለሰቦችን በአንድ ጥላ አሰባስቦ የያዘው ይህ ፓርቲ ከአሁን በፊት ይከተለው በነበረው አቋም እንደ ፖለቲካ ድርጅት የትግል ስልቱን ሰላማዊ አሊያም አመጽ ለማድረግ የተቸገረ መስሎ የቀረበበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም በተለይ በምርጫ ስነ - ምግባር ድርድሩ ላይ ለመካፈል አሻፈረኝ ካለበት ጊዜ አንስቶ እያደረገው ያለው እንቅስቃሴ ድርጅቱ ጤነኛ አለመሆኑን እያረጋገጠ መጥቷል፡፡

የአመጽ መንገድን መምረጡን በጉልህ እያሳዩ ከመጡት የፓርቲው ተግባራት መካከል አንዱ ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሲሉ ድርድሩን በተቀላቀሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ እያሳየ ያለው ንቀትና ጥላቻ ነው፡፡ በዚህም ግንባሩ ሊደብቀው እንኳ የተሳነው ኢ- ዴሞክራሲያዊ ባህርይው እየጐላ እንዲሄድ እና ገመናው በአደባባይ እንዲገለጥ አድርጐታል፡፡ ከአሁን በፊት በአንድ ኤምባሲ ጋባዥነት አዲስ አበባ ውስጥ ተዘጋጅቶ በነበረ የፖለቲካ ፓርቲዎች የውይይት መድረክ ላይ የምሳተፈው እዚያኛው ወንበር ላይ የተቀመጡት የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ ከወጡልኝ ብቻ ነው በማለቱ ራሱን ለሌሎች ፓርቲዎችና ለአዘጋጆቹ ዲፕሎማቶች ትዝብት አሣልፎ የሰጠው ፓርቲ ራሱን ከድርድር መድረክ ማግለሉ ሳያንሰው ሌሎቹ መግባት የለባቸውም የሚል አቋም እያራመደ መሆኑ በለበሰው ለምድ ሥር የተደበቀውን አውሬ ማንነት የሚያጋልጥ ከመሆን አላለፈም፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከከፍተኛ አመራር አባሎቹ እየወጡ ያሉት ዘገባዎችም እንዲሁ ፓርቲው የከሰረውን የአመጽ መንገድ መምረጡን እያመላከቱ መጥተዋል፡፡ ‹‹አሁን ባለው ሁኔታ ምርጫውን እናሸንፋለን ብለን አናስብም›› ፤ ‹‹ የኬንያው ዓይነት የሥልጣን መጋራት እንዲኖር እንፈልጋለን›› ፤ ‹‹ በማንኛውም ግፊት ተጠቅመን የሥልጣን ተጋሪዎች መሆን አለብን ›› የሚሉና የመሳሰሉ ባሩድ፣ ባሩድ የሚሸቱ ቃላትን ከአመራር አባላቱ ማድመጥና ማንበብ እየተለመደ መምጣቱ በርግጥም ሕሊና ላለው ሰው የሚረብሽ ነው፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ ገና ከጅምሩ ‹‹መድረክ›› የሚል ጠውም ቃል መጠሪያው አድርጐ ሲነሳ ለውይይትና ለድርድር ቅድሚያ የሚሰጥ መስሎ የቀረበው ይህ የግለሰቦችና የፓርቲዎች ጥምረት መድረኩን የውጊያ አሸዋ ገበታ ሊያደርገው አስቦ ከሆነ ራሱን ጭራሽ ከአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ እንዳስወጣ ከወዲሁ አውቆት ውድቀቱን በፀጋ መቀበል ይኖርበታል፡፡

እዚህ ላይ ግን የመድረክ መሪዎች መገንዘብ የሚኖርባቸው አንድ ሃቅ አለ፡፡ ማንኛውንም ግፊት ተጠቅሞ ሥልጣንን እይዛለሁ ብሎ መሞከር ፈጽሞ የማይታሰብበት ዘመን ላይ መድረሳቸውን በእርግጠኝነት ሊያውቁት ይገባል፡፡ የማይቻልበትም አካሄዱ በራሱ ኢ- ዴሞክራሲያዊ መሆኑ አንደኛው ምክንያት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ሥልጡን የሆነው የዚህ ዘመን አካሄድ በሰላማዊ ትግል በምርጫ ውድድር ተሳትፎ ከምርጫ ኮሮጆ በሚገኝ ድምጽ ብቻ ነው ሥልጣን መያዝ የሚቻለው፡፡ ከዚያ ውጭ አመጽና ትርምስን ፈጥሮ በመንግስት ላይ ጫና በማሳደር ሥልጣንን በአቋራጭ ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ሁሉ በባህርይው ከዴሞክራሲ መርህ ውጭ ከመሆኑም በላይ የአገርን ሰላምና ፀጥታ የሚያናጋ አደገኛ አካሄድ በመሆኑ በዚህ ዘመን ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ በእኛ አገር ካሁን በፊት ተሞክሮ ተቀባይነት እንደሌለው በተግባር መረጋገጡ ሌላው የመድረክ መሪዎች ሊያጤኑት የሚገባ ሃቅ ነው፡፡ ለዳበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕልውና መረጋገጥ በአገራችን የፖለቲካ ሂደት አዲስ ምእራፍ ከፍቶ ያለፈው ምርጫ 97 የታሰበውን ያህል ውጤታማ እንዳይሆን በማድረግ በአገሪቱ ታሪክ ልዩ ጠባሳ ትቶ ያለፈው የቅንጅት ፓርቲ በተሳሳተ አመራር ከሰላማዊ መንገድ ይልቅ አመጽን በመምረጡ እንደነበር ዛሬ ራሱን ‹‹ መድረክ ›› ብሎ የሚጠራው ጥምረት በውሉ የተረዳው አይመስልም፡፡ በዚያ ወቅት ተፈጥሮ የነበረው አደገኛ የፖለቲካ አዝማሚያ ውጤቱን እንቀበል ወይስ አንቀበል በሚል ትርምስ የቅንጅት አመራርንና አባላትን ለክፍፍልና ለፓርቲው ሕልውና መክሰም ብሎም እንደአገር ለሰው ሕይወት መጥፋትና ንብረት መውደም፣ የአመጽ መንገድን የመረጡ የፓርቲዉን አመራር አባላት ለእሥራት የዳረገው ከ10ሺህ እስከ 15 ሺህ የሚሆን ሕዝብንም ቢሆን መስዋእት አድርገን ሥልጣን እንይዛለን ይል የነበረው የቅንጅት የተሳሳተ አመራር እንደነበር ዛሬ ‹‹ መድረክ ›› ለአንድ ደቂቃ እንኳ ቢሆን ቆም ብሎ ማስታወስ ይገባዋል፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ ያኔ ጥይት የሌለው ሽጉጥ ይዘው መንግስትን ሲያስፈራሩ የነበሩት የቅንጅት አመራሮች እንጂ ኢህአዴግ እንዳልነበር

ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ እንዲያውም እንደአንጋፋና ጠንካራ ፓርቲነቱ ኢሕአዴግ በጊዜው የአምባገነንነት አቋም ቢያንፀባርቅ ኖሮ ብዙም ላይደንቀን ይችላል፡፡ በአፍሪካ የዴሞክራሲ ጀማሪ አገሮች ውስጥ ገዢ ፓርቲዎች የሚያንፀባርቁት አቋም በኢሕአዴግ ላይ አለመታየቱ የሚያስመሰግነው ነው፡፡ ኢህአዴግ ለሰላምና ለድርድር የሚሰጠው ልዩ ትኩረት ዛሬ የሕዝብን አድናቆትና ከበሬታ እየጨመረለት መጥቷል፡፡ አቋማቸውን ለማለሳለስና በሰላማዊ መንገድ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ጥረት የሚያደርጉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የዚያኑ ያህል ተቀባይነትን እያገኙ በመሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በአንፃሩ ጽንፈኛ አቋም በመያዝ ጊዜ ያለፈበትን የትግል ስልት እንከተላለን የሚሉ ቡድኖች በሕዝብ ዘንድ እየተተፉ ዛሬ እንደተራ የሽብርተኛ ቡድን የሚታዩበት ጊዜ ተደርሷል፡፡ እንደ ፓርቲ ጠንካራ ተቋማዊ መሠረት ሳይኖራቸው የምርጫ ቀን ሲደርስ ብቻ ሰርግ እንደተጠራ ተጋባዥ ራሳቸውን አሳምረውና ኳኩለው የሚቀርቡ ፓርቲዎች ራሳቸውን እንደበላይ በመቁጠር በመንግሥት ላይ ጫና እናሳድራለን በሚል ያዙኝ፣ ልቀቁኝ ማለታቸው ራሳቸውን ጭራሽ ወደማይመለሱበት አዘቅት ገፍቶ እያወረዳቸው ቢሄድ እንጂ ምንም እንደማይጠቅማቸው የመድረክ መሪዎች ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

ከቅንጅት ተሞክሮ ትምህርት መቅሰም ተስኗቸው እያንፀባረቁት ባለው ኋላቀር እና የሕዝብን ፍላጐት ያላገናዘበ የትግል አካሄድ መመለስ ወደማይችሉበት አዘቅት ራሳቸውን ቁልቁል እያወረዱ ለመገኘታቸው ተጨባጭ ማስረጃ የሚሆነው የአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ከተቀበሉት የጋራ የድርድር መድረክ ፓርቲውን ማግለላቸው ነው፡፡

በእስካሁኑ ሂደት ሌሎች ፓርቲዎች በጠረጴዛ ዙሪያ ከብበው በጋራና አገራዊ ጉዳዮች ላይ እየመከሩ ወዳለበት የድርድር መድረክ ፓርቲው ይመለሳል ብሎ ማሰብም ፍፁም ያከተመለት መሆኑን አንዳንድ ፍንጮች እያመላከቱ ነው፡፡ ለፓርቲው ልዩ የሕዝብ ግንኙነት ቢሊሚል ሆነው እያገለገሉ ባሉ አንድና ሁለት ‹‹ የግል ›› ጋዜጦች የተጋጋለ የማስታወቂያ ዘመቻ የተነሳ

በመጪው ምርጫ ላይ ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናል የሚል ግምት አድሮበት የነበረው የዲፕሎማቲኩ ማኅበረሰብ ፓርቲውን አሳምኖ ወደድርድሩ ለማስገባት ሲያደርገው የነበረው ጥረት መና እየሆነ መጥቷል፡፡ የ‹‹ መድረክ ›› አመራሩ ወደ ድርድር ላለመመለስ ያሳየው ግትርነት በውል ሳይረዳው ቀርቶ እንጂ ተወደደም ተጠላም በዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ዘንድ የነበረውን ከበሬታ አሣጥቶታል፡፡ ፓርቲው ለዴሞክራሲያዊ ድርድርም ይሁን ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ ራሱን እንዳላዘጋጀ በሂደት ለዲፕሎማሲ ማኅበረሰብ ራሱን አጋልጦ ሰጥቷል፡፡

በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ይልቅ የተሻለ ዋጋ የሚሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደመሆኑ አሁንም ‹‹ መድረክ ›› ሊገነዘበው ያልቻለው ወይም ሊቀበለው ያልፈለገው እውነታ የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተሳሰብ ከምርጫ 97 በኋላ በእጅጉ መለወጡን ነው፡፡ ይህንን በተጨባጭ ለመገንዘብ ካስፈለገ ሕዝቡ በ2000 ዓ.ም. በተካሄደው የማሟያና የአካባቢ ምርጫ ወቅት ያሳየው የሰከነ አካሄድ ነው፡፡ ሕዝቡ ከአመጽ ይልቅ ሰላማዊ አካሄድን በመምረጡም ዛሬ በፓርቲዎች መካከል እየተካሄደ ያለውን ሰላማዊ ድርድር በአንክሮ እየተከታተለው፣ ከዓለም ዴሞክራሲያዊ አገሮች ተሞክሮ ወደፊት በፓርቲዎች የጋራ ስምምነት የሚወጣውን የስነ ምግባር ደንብ በጉጉት እየጠበቀው ይገኛል፡፡ ይህንን በውል ያልተገነዘቡት መድረኮች ዛሬ በዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡ ትዝብት ውስጥ የጣላቸው ገታራ አካሄድ በሕዝብ ዘንድም ተቀባይነትን እያሳጣቸው ነው፡፡ በመሆኑም ፓርቲው ከወዲሁ ለሽንፈት የሚያበቃውን ካርድ አስቀድሞ መቀበሉን አምኗል፡፡ ይህ አካሄዳችሁ ነገ ጭራሽ እርቃናችሁን የሚያስቀራችሁ አፍራሽ ተግባር መሆኑን ተገንዝባችሁ ዘመኑ ለሚጠይቀው ሥልጡን የፖለቲካ ትግል ስልት ራሳችሁን አዘጋጁ፣ ይህንንም ካላደረጋችሁ ፍፃሜያችሁ አያምርም የሚለው መልእክቴ ነው፡፡ ሰላም!